# Union of Tigreans in North America (UTNA)
## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
UTNAINK@aol.com

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703

---

### ሻዕቢያ በሃገራችን ላይ ያነጣጠረውን ሴራ አስመልክቶ
### <u>ከትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ) የወጣ መግለጫ</u>

***ሻዕቢያ ዘርፈ-ብዙ ፀረ-ኢትዮጵያ ሴራና ተንኮል እየጎነጎነና እያጠነጠነ መላ ትኩረቱን፣ጊዜውንና አቅሙን በመጠቀም ኢትዮጵያን መውጋት፣ መጎንተል፣ማተራመስና ማወክ እንደ መደበኛ ተልእኮውና ዓይነተኛ ስራው በመያዝ በሙሉ ሃይል ከተሰማራበት እንሆ ዓመታት ተቆጥረዋል።በዚሁ እኩይ ተግባሩና ዓላማው የሩቅና የቅርብ ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎችን በመመልመል፣በማስተባበር በማቀናጀት በማሰልጠን፣በማስታጠቅና በማሰማራት የኢትዮጵያን መፈራረስ የማየት የቆየ ህልሙን እውን ለማድረግ የማይፈነቅለው ድንጋይና የማይቀነጥሰው ቅጠል የማይምሰው ጉድጓድ የለም!!***

***የሸረበውን አጥፊ ንድፍ ያሳኩልኛል ብሎ ያመነባቸውን በጥላቻ፣በጠባብነትና በትምክህት የተበከሉ የውስጥ ሃይሎችንና ግብረአበሮቻቸውን በየወቅቱ እያሰማራ በሰላማችን በልማታችንና ደፋ ቀና በምንልለት ታዳጊና ጎልባች የዴሞክራሲ ሂደታችን ላይ ደንቃራ መፍጠርን አበክሮ ገፍቶበታል።***

***የዚህ የፀረ ኢትዮጵያ እርጉም ተልእኮውንም አድማስ በማስፋት ሻዕቢያ ከፈፀማቸው አያሌ ሰይጣናዊ ተግባራት መካከል፡-***

- ***ሻዕቢያ ከዛሬ ዘጠኝ ዓመት በፊት*** 1990 ***ዓ.ም በእብሪት በመነሳሳት የሃገራችንን ሉዓላዊነት ደፍሮ ድንበራችንን ጥሶ ግልፅ ወረራ በመፈፀም በሺዎች የተቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎቻችን አፍኗል፣አፈናቅሏል፣ገድሏል።***
- ***ሻዕቢያ እኩይና አረመኔያዊ ጦርነቱን ከከፈተ በኋላና ከመከፈቱ በፊት ከተራ ኮንትሮባንዲስነት፣የጥቁር ገበያ ደላላነት፣ኤኮኖሚያዊ አሻጥር፣ድንበር ዘለል ጭብርብሮሽ ጀምሮ ሰላማዊ ዜጎቻችንን መረሸንና ማፈን፣ህፃናትን በመርዝ ቦምብ መደብደብ፣ እህቶቻችንን መግሰስ፣ንዋዬ ቅዱሳትን መዝረፍ፣ቅርሳቅርሶቻችንን መመንተፍ ይሁነኝ ብሎ ገፍቶበታል።***
- ***የአልጀርሱ ስምምነት ከተፈረመ ወዲህ የፀጥታ ቀጠናውን አልፎ የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሩ ዘቦችን ከቁብ ባለመቁጠር ድንበር እየጣሰ ንፁሃን ዜጎችን በማፈንና በመግደል ፈንጂ ቀብሮ ህፃናት፣ሴቶችንና አረጋውያንን ሰለባ በማድረግ የንብረት፣የእንስሳትና የተፈጥሮ ሃብታችንን ዘርፎና አሸባሪዎችን አሰርጎ በማስገባት ጥቃት እየፈፀመብን ይገኛል።***

- *ከጥቂት ወራት በፊት የፀጥታ ቀጠናውን አትለፍ የሚለውን በፊርማው ያፀደቀውን ውል በእብሪትና በማንአለብኝነት ጥሶ ብረት ለበስ ሰራዊቱ አስገብቶ የጋራ ስምምነቱ ከሚፈቅድለት ውጭ ታጣቂ ተዋጊ ሃ ይሉን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ያለአግባብ በማስጠጋት የፀብ አጫሪነቱን ሰይፍ እንደወደረ ይገኛል።*
- *በተለያዩ ክልሎች የውስጥ ፀረ-ሰላም ሃይሎችን እያስታጠቀና እያሰረገ ኢትዮጵያን የማመሰቃቀል እኩይ ዓላማውን እውን ለማድረግ ሳይታክት ገፍቶበታል።*
- *በሞቃዲሾ መሸገው ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ምድር የጠበበችባቸውን ያህል በእዩኝ እዩኝ ድንፋታ ያበጡትንና በዓለም ሽብርተኞች ተከበው የነበሩትን የሶማልያ ፅንፈኞችና ተስፋፊዎችን አቅፎና ደግፎ ከአይዞህ ባዩቹ ጋር በመሆን ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ፀጉር አስታጥቆ ሲያስፏልላቸው የነበሩትን ሃይሎች ፉከራቸው ሚሸሸ ደብቁኝ ደብቁኝ በማለት በዓለም ፊት የሽንፈት ፅዋቸውን እንዲጎነጩ ብሎም እንዲጋቱ ገፋፍቷቸዋል።*
- *ሻዕቢያ የመንግስታዊ ሽብርተኝነቱን መሰሪ ድርጊት በማፋፋም በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ከተሞች፣መስሪያ ቤቶች፣ድርጅቶች፣የህዝብ መገልገያ ስፍራዎችና አደባባዮች ላይ የፈንጂ ቀበራ፣የቦምብ ፍንዳታና የሽብር መንዛት ተራ ወንጀል ላይ በመሰማራት በወገን ህይወትና ንብረት አደጋ በመጣል በሃገር ሰላምና ደህንነት ላይ አለመረጋጋትን በመፍጠር ላይ ይገኛል።*
- *በቅርቡ በቃጣው አስነዋሪ ድርጊት በኢትዮጵያ የአፍሪቃ አህጉራዊ መዲናነት ላይ ያነጣጠረ መሰሪ ድሎታ አካሂዶ በህዝብ ፅኑ ትብብርና በነቃ የፀጥታ ሃይሎች ክትትልና ጥበብ የጎነጎነው ሴራ እንደ ጧት ጤዛ ረግፏል።*
- *ሻዕቢያ በጥፋት ጉዞው በመንደርደር ሃገራችን የዓለምን ትኩረት ስባ መፃኢውን የሚሊየንየም በዓል ባሽብራቂ ሃገራዊ ክብርና ሞገስ በደመቀ ሁኔታ ለማክበር በምታሸበሽብበት በአሁኑ የብሄራዊ ትርዕይቱ ዋዜማ የሰው ልጅ እናት በሆነችው በድንቅነሽ የትውልድ መንደር በኢትዮጵያ የአፋር ክልል በሰላማዊ መዝናናት፣እይታ፣ጥናትና ጉብኝት ላይ በነበሩት አውሮፓውያንና ኢትዮጵያውያን ላይ አፈና በማካሄድ የሃገራችንን ገፅታ ጥላሸት በመቀባት በጎ ጥረታችን ሁሉ ፍሬ አልባ እንዲሆን ተራ የምንቀኝነትና የጠላትነት ደባ ፈፅሞብናል።*
- *ሻዕቢያ ከወሰን እስከ መሃል አገር እንዲያም ሲል በውጭው ዓለም በከፈተብን ዙርያ-መለስ አናቋሪ ፀብ ጫሪ የፈጠራ ፕሮፖጋንዳና ሃሰትን የተላበሰ ፀረ-ኢትዮጵያ የሚዲያና የዲፕሎማሲ ሰይጣናዊ ዘመቻ እያራመደና እየነዛ በሰላማችን፣በልማታችንና በመልካም አስተዳደር ጥረታችን ላይ የጉሮሮ አጥንት ሆኖብናል።*

*በሻዕቢያ መንግስት በኩል ይህ ሁሉ የተንኮል ሸረባ፣ ደባና አጥፊ ተግባር ቢደነቀርብንም የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ዋናውና መሰረታዊ ጠላታችን በሆነው ድህነትን ከስረ መሰረቱ በማስወገዱ ዓቢይ ጉዳይ ላይ በማነጣጠር ልማት ሰላምና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያችን አብቦና ለምልሞ ለፍሬ እንዲበቃ ልዩ ትኩረት ሰጥተው በመረባረብ ላይ መሆናቸውን በአንክሮ እናስተውላለን።በሌላ በኩልም በኤርትራ በኩል የተደቀነብንን ፈታኝ ሁናቴ ለመፍታት የኢትዮጵያ መንግስት ያቀረበው ባለ ኣምስት ነጥብ የሰላም ሃሳብና የዓለም ህብረተሰብ ከጎናችን እንዲቆም ለማብቃት የተካሄደውን እልህ አስጨራሽ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት የሚሞገስ*

ነው።ይሁንና ይኸንን የተቀደሰ የኢትዮጵያን የሰላም ፍለጋ ጥረት ከምንም ባለመቁጠር የሻዕቢያ አመራር ነጋ ጠባ ልማታችንን የሚያስተጓጉል፣ሰላማችንን የሚያደፈርስና የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ልፋታችንን የሚያደናቅፍ የዘወትርና የማያሰልስ ዘመቻና ጥቃት እየሰነዘረብን ዓላማችንን ሙሉ በሙሉ ማሳካት አይቻለንም።

አደፍራሽ እያለ ንፁህ ውሃ መጠጣት ያለመቻሉን ከባድነት ስናጤን ምንም እንኳን የሻዕቢያ አመራርን ከይሲ ተግባር ነገ በምን ላይና በምን ሁኔታ፣የት፣መቼና እንዴት በማን ላይ እንደሚፈፅም በትክክል መተንበይ ባይቻልም የዚህ ሽብርተኛ ኣካል ተፈጥሯዊ ባህርይ በመሆኑ ክስተቱ እንደሚቀጥል ግን በእርግጠኝነት በመናገር ሻዕቢያ በአዲስ ዘዴና መላ በኢትዮጵያ ላይ ያልተቋረጠ ጦርነት እያካሄደ ለመሆኑ በእማኝነት መቁጠር ያስችላል።

እንደእውነቱ ከሆነ የሻዕቢያ አመራር በ1990 ሰኔ ወር ላይ ድንበር ጥሶ ሉዓላዊነታችንን ደፍሮ በዕብሪት የከፈተብንን ጦርነት ከሁለት ዓመት በኋላ በጀግናው የኢትዮጵያ ሰራዊት ሃያል ምት ዳግም ሙሉ በሙሉ በማያንሰራራበት መልኩ ክፉኛ ድባቅ ቢመታም የጦርነት ታክቲኩን በየጊዜው በመለዋወጥ ወትሮም የተነሳሳለትንና የቆመለትን ኢትዮጵያን የማተራመስ ብሎም የማፈራረስ የጥፋት መተክላዊ ዓላማውን የማሳካት ስትራተጂካዊ ግቡን ለመምታት የሚያስችለውን “ተያይዘን እንውደቅ፣ተያይዘን እንጥፋ” በሚለው የጦርነት ዘዬው ውጊያውን በውሱን መልኩ ገፍቶበታል።

በመሆኑም የሁኔታውን አሳሳቢነትና አደገኛነት እንዲሁም በሰላማችን፣በልማታችን፣በመልካም አስተዳደር ጥረታችን በሃገራችን ፀጥታ ላይና በህዝባችን ስክነትና መረጋጋት ላይ እየፈጠረ ያለውን አሉታዊ ጫና በማጤን የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ በጉዳዩ ላይ የሚከተለውን አቋም ወስዷል።

1. ሽብርተኛው የሻዕቢያ አመራር በቀቢፀ ተስፋ የሃገራችንና የህዝባችንን ጥረት በተገኘው አጋጣሚ ለማሰናከል የሚያደርገውን መቅበዝበዝና አስነዋሪ የጥፋት ድርጊት አምረን እንኮንናለን፣ መንግስት ይኸንን ሙከራ ለማክሸፍ ለሚወስደው ርምጃ የተሟላ ድጋፋችንን እንደምንሰጥ በሙሉ ልብ እናረጋግጣለን፣
2. የሃገራችን ትኩረትና የልማትና የመልካም አስተዳደር እነፃ ተግባር ኢትዮያ ሰላሟ በአስተማማኝ ሳይረጋገጥ በሻዕቢያ ስውርና ግልፅ ሴራ እየተናጠ ከቶውኑ ሊሳካ ስለማይችል መንግስት እስካሁን ይዞት የተጓዘውን ኤርትራን የሚመለከት ፖሊሲ እንደገና በመመርመር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ነፃነትና የህዝቦቿን ክብርና ማንነት ሙሉ በሙሉ በሚያረጋግጥ መልኩ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የተዋደደ አዲስና ስር ተከል ፖሊሲ ቀርፆ ለተግባራዊነቱ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ በአፅንኦት እንጠይቃለን፣
3. ለመቁጠር በሚያታክት የኤርትራ ፀብ ጫሪነትና ዕብሪት በተለያየ መልኩ በተደጋጋሚ የተሸራረፈውና የተጣሰው የአልጀርስን ስምምነት አክብሮ መቀጠሉ ጥቃትን አሜን ብሎ መቀበልን ስለሚያመለክትና ሙሉዕነት በተጓደለ ስምምነት ተገዥ መሆንን የግድ ስለማይል የአልጀርሱ ስምምነት በኤርትራ እምቢተኝነትና ማንአለብኝነት

እንደፈረሰ ተቆጥሮ ኢትዮጵያም ከንግዲህ እንደማትቀበለው በመንግስት በኩል በማያሻማ መልኩ ተገልፆ አቋም እንዲወስድበት እጥብቀን እንጠይቃልን፣

4. ሽብርተኛው የኤርትራ መንግስት በቅርቡ የገታችውና በቁጥጥሩ ስር የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ሻዕቢያ ወገኖቻችንን በገዛ አገራቸው በነፃነት የመንቀሳቀሱን ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን ተጋፍቶ የሃገራችንን ሉዓላዊነት በመድፈር ዓለም አቀፍ ህግን የጣሰ አረመኔያዊና ዕብሪተኛ ተግባር እያወገዝን ታጋቾቹ በሰላም ተለቀው የኢትዮጵያ መንግስት የዜጎቹን መብት፣ክብርና ማንነት እንዲሁም የሃገሪቱ ን ሉዓላዊነት የሚያስከብር ሁሉን አቀፍ አስቸኳይ ርምጃ እንዲወስድ በአንድ ድምፅ እንጠይቃለን፣
5. የኢትዮጵያ ህዝብና የተወካዮች ምክር ቤትም የሃገሪቱ ከፍተኛ አካላት እንደመሆናቸው መጠን አሁን በሃገራችን ላይ ያንዣበበውን የልተቋረጠ የሻዕቢያ አመራር ሴራ ተወግዶ ዘላቂ ሰላም ዴሞክራሲና ልማት ይፋጠን ዘንድ ለሚያደርጉት ርብርብ ከጎናቸው የተሰለፍን መሆናችንን እናረጋግጣለን፣
6. ወትሮውም በማይናወጠው ሃገራዊ ፅናቱና ጀብዱ የገነነው ጀግናው የኢትዮጵያ ሰራዊትም በአሁኑ ወቅት በሻዕቢያ ተንኮል የተሸረበውና በሃገራችምን ልዩ ልዩ ማዕዘናት የቆበቆበው ሴራ ዛሬም እንደወትሮው በሚያስመካ የወገንና የሃገር ፍቅርና ወኔ ለመመከት በሚያሳየው ቆራጥ አቋምና ዝግጁነት ምንጊዜም የማንቀጠበውን ድጋፋችንን እንገልፃለን፣

በውጭ ሃገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወገናችንም ውዲቱ ሃገራችን ኢትዮጵያ ከድህነት አረንቋ ለአንዴና ለሁሌም ወጥታ ወገኖቻችን እፎይታ አግኝተው የሰላም፣የልማትና የመልካም አስተዳደር ጣዕም እንዳያጣጥመው የጎን ውጋት የሆነው የሻዕቢያ አመራር የሚያደርገውን የማደናቀፍ ተግባር ለማክሸፍ የበኩላችንን ብሄራዊ ግዴታ ዛሬ እንድናበረክት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፣

በሻዕቢያ አመራርና የኢትዮጵያን ልማት ማየት በማይሹ ሃይሎች ዛሬ በወገናችን ላይ የተደገሰው የጥፋት ድግስ፣ጦርነት በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ ሊቆሰቆስ የሚችል ሰይጣናዊ ክስተትና እንደ ሰላም አጋር የማያሻው የጥፋት ተልእኮ መሆኑን ለአፍታ እንኳን ሊዘነጋ አይገባውም። ስለሆነምይህ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ የፈሰሰው በሃገራችን ላይ በሻዕቢያ ግንባር ቀደም ተዋናይነትና አስተባባሪነት በመካሄድ ላይ ያለው ውስብስብ የጥፋትና የጥቃት ሴራ እንቆቅልሽ በአስቸኳይ ሁነኛ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ፣ ሳይውል ሳያድር ሃገራዊ መፍትሄ የሚሻ አንገብጋቢ አጀንዳ መሆኑን ያለምንም ማመንታት ግንዛቤን ሊቸረው የሚገባ እጅግ አደገኛና አሳሳቢ ብሄራዊ ጉዳይ ነው እንላለን።

ባጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥም ይሁን በውጭ፣በሃገርና በመንግስት ላይ የሚካሄደው ዘርፈ-ብዙ ውስብስብ ሸር፣ሴራና ጥቃትና በተንኮል የተተበተበ መሰሪ ዘመቻ ያለምንም ጥርጥር የሽብርተኛው የሻዕቢያ እጅ የተነከረበት ባለ ብዙ-ገቢር፣አንድ-ወጥ ትራጂ-ድራማ አምሳልና አካል በመሆኑ ሃገርንና ወገንን የመታደግ ሃላፊነት የጎላና ወቅታዊ ምላሽን የሚሻ መሆኑን እናስገነዝባለን።